YEHOOLACHIN ETHIOPIAN COMMUNITY IN COLORADO
**የሁላችን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኮሎራዶ**

# የአዲስ ዓመት መልዕክት

በአገራችን ለ25 ዓመታት ሰፍኖ የቆየው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ጥያቄ ያቀረቡ ወገኖቻችንን በጠራራ ፀሐይ ያለፍርድ እየገደለና በአሥር ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ኢትዮጵያውያንን በየማጎሪያ ካምፑ እያሰቃየ ባለበት በአሁኑ ወቅት አዲሱን ዓመት በመሪር ሐዘን ነው የምንቀበለው:: መጪው ዘመን ሕዝባችን ይህንን አስከፊ ሥርዓት ከጫንቃው ላይ አሽቀንጥሮ በመጣል ፍትህ እኩልነትና ነፃነት የሰፈነባት፣ ዘረኝነት ከአገራችን ምድር ተወግዶ አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ የምንመሠርትበት ዘመን እንዲሆንልን ምኞታችን ነው፤ እምነታችንም ጽኑ ነው::

ኮሚዩኒታችን፣ ይህ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈጸመ ባለበት በአሁኑ ወቅት ዳር ሆኖ በገለልተኝነት መመልከቱን ኢትዮጵያዊ ባሕላችን ስለማይፈቅድልን፤ የሁላችን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኮሎራዶ የnon-profit ተቋምነቱን ሳይለቅ፣ በመመስረቻ ጽሑፋችን ላይ ስለሰብዓዊ መብት የተጠቀሰውን በማንተራስና መሠረት በማድረግ ለሚደረገው የሞት ሽረት ትግል የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ወስኗል::

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ቅድሚያ ትኩረትና አጽንዖት በመስጠት በኮሎራዶ አንድ የጄኖሳይድ[i] መረጃ ዩኒት በማቋቋም፣ መረጃ በመሰብሰብ፣ በማሰራጨትና አርካይቭ በማድረግ ለወደፊቱ ትውልድ እንዲተላለፍና በሕግ ተጠያቂ ለሚሆኑ አካላት እንደመረጃ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል የአዲሱን ዓመት ሥራውን በዚሁ ይጀምራል:: ይህንኑ በፌስቡክና በቫይበር በምንከፍታቸው ገጾች በዝርዝር እናሳውቃለን::

በቀጣይም በከተማችን ከአንድ በላይ የኮሚዩኒቲ ማሕበር የመኖሩን አስፈላጊነት ስለማናምንበት፣ ለድርጅታችን አግባብ ያለው ስያሜ በመስጠትና ሙሉ በሙሉ አዳዲስ የአመራር አባላትን በማስመረጥ ለሚደረገው ትግል የበኩላችንን አስተዋጽዖ ለማድረግ ወስነናል:: ማሕበረሰቡም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግልን እርግጠኞች ነን::

የሁላችን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በኮሎራዶ

የሁላችን
YEHOOLACHIN

[i] የዘር ማጥፋት የሚለው ለእንግሊዝኛው genocide ትክክለኛ ትርጉም ባለመሆኑ ቃሉን በግዕዝ ፊደል እንጠቀማለን::